# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP

ነሐሴ 14 ቀን 2005 ዓ.ም.

*ለክርስቲያን ወገኖቻችን ማሳሰቢያ*

ሀይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው፤ ፖለቲካና ሀይማኖት አይደባለቁ በሚሉት መሰረታዊ መርሆዎች የሚያምነው ኢሕአፓ በወያኔ የተቀነባበረውን ከፋፍለህ ግዛና ጸረ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ዕቅድ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ነቅተውና በጋራ ሆነው እንዲያከሽፉ በእጅጉ ያሳስባል፤ የከበረ ጥሪም ያደርጋል ።

ወያኔ የሙስሊም ወገኖቻችንን መብት ነፍጎ፤ በላያቸው ላይም ባዕድ እምነት ሊጭንና በሀይማኖት ጉዳያቸው ላይ ጣልቃ በመግባቱ ሳቢያ የጀመሩት የሚደገፍ የተቃውሞ እንቅስቃሴን ለማክሸፍ ያልሞከረው ሴራና ያልከፈተው ዘመቻ የለም። በተለይም ክርስቲያኑን ኢትዮጵያዊ ለማስፈራራትና ከወገኖቹ ሙስሊሞች ጋርና ጎን እንዳይሰለፍ ለማድረግ የሀሰት ቪዲዮውችንም እየቀረጸ፤ እንቅስቃሴውን ሽብርተኖች ከሚላቸው ሊያቆራኝ እየሞከረ፤ አፈና እያካሄደ ወዘተ በመጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳዎች የታጀበ ሰፊ ዘመቻን ከፍቷል። ዋልድባን ለባዕዳን የሸጠው ወያኔ ክርስቲያኑን የደለለ እየመሰለው ድሮ በታሪክ ተቃጠሉ የሚላቸውን ቤተክርስቲያኖች መስራት የሚልም እደናጋሪ ቅስቀሳ መጀምሩንም እናስተውላለን። ዋልድባ ሲደፈር ለሰልፍ ብቅ ብለው የማያውቁና በወያኔ ቁጥጥር ስር የገቡ የባዕድ ቤተ ክርስቲያኖች ሀላፊዎችም የዚሁ ጸያፍ ዘመቻ ተባባሪ ሆነው ጸረ ሙስሊም ቅስቀሳውን መጀመራቸውንም ታዝበናል። ይህንን በዝምታ የምናልፈው አይደለም። ጽንፈኝነትን መቃውም--ከየትም ይምጣ ከየት--የሚገባ ቢሆንም መብታችን ይከበር የሚል እንቅስቃሴን ግን በወያኔ ቀስቃሽነት በጽንፈኛነት ፈርጆ ለወያኔ ተንኮል ሰለባ መሆን የሚገባ አይደለም። ወያኔ የሀሰት ወረቀቶችንና ክሶችን አሰራጭቶ አልሰራ ሲለው ከዚህ ቀደም እንዳደረገው ሁሉ ቤተክርስቲያኖችን አቃጥሎና ምዕመናንም ገድሎ በሙስሊሞች ላይ ለማላከክ የሚጥር መሆኑን መጠበቅ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን በሀገርም በውጭ ሀገርም በጎጥ ሳይቀር ከፋፍሎ የሚያፈራርሰውና በቅጥረኞቹ ቁጥጥር ስር የሚያስገባው የአማኞች ዋና ጠላት ወያኔ እንጂ መብታችን ይከበር ያሉና መስዋዕትነትንም እየከፈሉ ያሉ ሙስሊም ወገኖቻችን አይደሉም። በፍትሓዊው እንቅስቃሴ ውስጥ ሰርገው ገብተው ጥላቻና እልቂትን የሚጋብዙ አስመሳዮችና ጽንፈኞች ደግሞ ተልዕኮአቸው ወያኔያዊ ነውና እነዚህንም ማጋለጥና ከሕዝብ ትግል ማራቅ አስፈላጊና ወቅታዊም ነው።

ሕዝብ ከህዝብ የሚያጣላውን የወያኔ ዘመቻ ሕዝብ ክርስቲያን ከቶምና መቼም ቢሆን መደገፍ የለበትም። የወያኔን ተንኮልና ሴራ በሀይማኖት ሽፋን ሊይራግቡና ሕዝብን በሀይማኖት ሊከፋፍሉ የተነሱትንም -- በውጭ ሀገር ሆነ በሀገር ቤት-- አጥብቀን በጋራ እንድንታገላቸው ኢሕአፓ ጥሪውን ያስተላልፋል። ምዕመናን መብታችውንም ቤተ ክርስቲያኖችንም መስጊዳቸውንም ማስከበር አለባቸው። ክርስቲያኖች ጸረ ሕዝብ ጸረ ኢትዮጵያ ከሆነው ከወያኔ ጎን ሳይሆን ከሙስሊም ወገኖቻቸው ጎን በመቆምና የተጀመረውንም ትግል በማጀብ ለመላ ኢትዮጵያዊ ዜጋ መብት እንዲታገሉም እነሆ ዳግም ጥሪው ቀርቧል።

ጸረ ሕዝብ ሀይል የሆነው ወያኔ ነው!
ለወያኔ ከፋፋይ ተንኮል ሰለባ አንሁን!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል !!!



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email** **ESPIC@aol.com**
**Website** **WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 22**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**